# <u>ወያኔው ደብረጽዮን የትግራይ ሕዝብ በማንነቱ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ሲታይ ነበር ሲል ትግሬዎች ከደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች ጋር አመሳስሎአቸዋል</u>

<u>ጌታቸው ረዳ (Ethiopian Semay)</u>

ወደ ርዕሳችን ከመግባታችን በፊት በቅርቡ ስለ አስገረመኝ ዜና ጥቂት ልበል። አብይ የሚባለው ደማሪ ስለ ምሕረት ሲናገር፤ የቀድሞ የደርግ መሪው መንግሥቱ ሃይለማርያም ጋር ሲደርስ ሕገመንግሥቱ ስማይፈቅድ ምሕረት አያገኙም ይላል። ለምን? ቢባል ሕገ መንግሥቱ በቀይ ሽብር የተካፈሉትን ምሕረት አይሰጥም ይላል። ሕገ መንግሥቱ ያረቀቁት ደግሞ እነማን ናቸው? ብለን ብንጠይቅ ከቀይ ሽብር እኩል ያልተናነሰ ግድያ እና ሽብር ክሕደት የፈጸሙ በነጭ ሽብር የተካፈሉት "መንሽቪኾች እና ቦልሸቪኮች" ወያኔዎች፤ ሻዕቢያዎች ፤ ኢሕአፓ ነባሮች፤ ኦነጎች የመሳሰሉ ሽብርተኞች የረቀቀ ሕገመንግሥት ነው።ታዲያ አብይ የተባለው ደማሪ **<u>ነጭ እና ቀይ</u>** ሽብር በሚል ለያይቶ ያንን ነጻ ያንን ወንጀለኛ የሚያደርግ ማስረጃ በምኑ ችሎት ፈትሾት ነው ሕገ መንግሥት እያለ ያለው ሊያምነው የቻለበት ድምዳሜ?

እንዲህ ያለ ድምዳሜ ሊደርስ የቻለው በቀይ እና በነጭ ሽብር ብቻ የተካፈሉት ተገዳዮች ናቸው ወይንስ ስም ያልተሰጣቸው ወንጀለኞች እና ሽብርተኞችም ጭምር ታግደዋል? ሕገ መንግሥት ተብየው ከአዋጅ በላይ ከሆነ፤ በአዋጅ የመዘገባቸው ኦነግን ያክል በዘር ማጥፋት የተካፈሉ ከወንጀል ነፃ አድርጎ ምሕረት ሲሰጣቸው 'ሕገመንግሥቱን የሚጻረር' ወንጀል የፈጸሙ የድርጅት ሃላፊዎች አዲስ አበባ ገብተው ባንዴራቸውን ሲያውለበልቡ አብይ በየትኛው የሞራል መመዘኛ ነው እነዚህን ሊያስገባቸው የቻለው? እሱ እራሱ ያዋቀረው የስለላ ድርጅት ለዚህ ሁሉ ግፍ እንዲፈጽም በምን መመዘኛ ነው ሕገ መንግሥቱ የፈቀደለት? ሕገ መንግሥት ያልፈቀደው ወንጀል ፈጽመናል እያለ እራሱ በሕዝብ ፊት 'ይቅርታ እየጠየቀ" ሌላው ግን ሕገ መንገሥቱ ምህረትና ይቀርታ አይፈቅድለትም ብሎ የማለት ሞራሉ ማን ነው የሰጠው? በሌላ ርዕስ እመለሳለሁ፡ አሁን ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ።

ለዓሸንዳ በዓል ተሳታፊዎች እና እንግዶች መቀሌ ከተማ ተገኝቶ የወያኔው ደብረጽዮን ገብረሚካኤል በትግርኛ ቋንቋ እንዲህ ሲል ተናግሯል። (ሕዝቢ ትግራይ ብቋንቁኡን ብመንነቱን ሓፈሩን ተዋሪዱን ከም አሉታዊ ዜጋ ተቖጺሩን ክነብር ዝተገደደሉ ናይ ታሪኽ አጋጣሚ ነይሩ እዩ") "የትግራይ ሕዝብ በቋንቋው እና በማንነቱ ኣፍሮ እና ተዋርዶ በገዛ አገሩ እንዲኖር እንደ አሉታዊ ዜጋ የተቆጠረበት የታሪክ አጋጣሚ ነበር" ይላል። ወደ ትንታኔአችን ከመግበታቸን በፊት "አሉታ" ማለት "ውሸት" ማለት ነው። አሉታ ደግሞ በሕክምና '**<u>ትርፍ አንጀት'</u>** እንደማለት ነው። የማይፈለግ ክፍል ማለት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ 'አፍራሽ' ማለት ነው። አጠቃላይ በፖለቲካ አጠቃቀሙ ሲተረጎም 'አሉታዊ' ማለት የማይፈለግ **<u>'ተቀናሽ'</u>** ማለት ነው። በፎቶግራፊክ ሕግ ስንሄድ ደግሞ ነጋቲቭ ፊልም ማለት ከተፈጥሮአዊው (ኦሪጂናሌው/የጥንቱ የጥዋቱ/) የያዘው ቅርጽ ሕብሩ እና ብርሃኑ እንዳለ

ሳይሆን በተገላቢጦሽ የሚታይ ቅርጽ ማለት ነው። እንግዲህ ምስል እንጂ ዋናው አይደለም ማለት ነው። አስቀድሜ እንደገለጽኩት በፖለቲካው ስንኝ አሉታዊ ማለት ”የማይፈለግ” “ተቀናሽ ማለት ነው። በግልጽ አማርኛ እና እንግሊዚዝኛው ትርጉም negative means “Reject, refuse to accept” ማለት ነው። ለምሳሌ“The Bill was negative by 130 votes to 90” የቀረበው ሰነድ 130 ለ90 ውድቅ ሆኗል ሲል 130 ድምጽ ሰጪዎች ሰነዱን አንቀበለውም ብለው ጥለውታል ማለት ነው። በዚህ መልክ ድምፅ ሰጪዎች የሰነዱ አሉታዊ ገጽታ /ጤናማ ስላልሆነ/ ስላለውደዱት ከሌሎች ሰነዶች ነጥለው አንቀበልም ብለዋል ማለት ነው። በዚህ ትርጉም የተነፈገ ማለት ነው።

ጥልቅ ትርጉም ልሰጣችሁ የፈለግኩበት ምክንያትም የደብረጽዮን አፈቀላጤዎች ለሚሰጡት የሽፋን ምክንያት በር ለመዝጋት በሚል ነው። እንቀጥል። በሂሳብም ነጋቲቭ/አሉታ/ የሚለው የሚነግረን ትርጉም “ካንድ ጥቅል የተቀነሰ ክፍል/አካል ማለት ነው”። ታዲያ ደብረጽዮን የትግራይ ሕዝብ ከመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በማንነቱ አሉታዊ ማሕበረሰብ ተብሎ የተነጠለበት/ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ ሲታይ የነበረበት የታሪክ ወቅት ነበር ሲል ቀጥተኛ ትርጉሙ ትግሬዎች በማንነታቸው “ትግሬዎች” ስለሆኑ ብቻ “አይፈለጉም’ ነበር” “ይገለሉ” ነበር ስለሆነም በሰብእናቸው እንዲያፍሩ ተደርጓል ይላል። እንዴት? ለምንስ ነው? ማን ነውስ በማንነታቸው ተነጥለው እንዲታዩ ያደረጋቸው?

ባዓሉን ለማክበር በተገኘበት ‘አሸንዳ’ የተባለው በዓልም እንደሆነ በታሪክ በፍጹም በማንኛውም አገዛዝ ዘመን ታግዶም ተከልክሎም አይታወቅም። ምንስ ለማት ፈልጎ ነው በዚህ በዓል እንዲህ ያለ ቀፋፊ ውሸት ሊዋሽ የገፋፋው? የሚል ጥያቄ ለመመለስ ደብረጽዮን ማን መሆኑን ከማሕደሩ ብንመለከት የውሸት እና የቅጥፈት ባሕሪው በግልጽ በሚከተለው ማሕደሩ ብንመለከት የመዋሸት ምንጭ መቸ እንደጀመረ ሊረዳን ይችላል።

<u>**ኮለኔል ፍስሃ ሃይለማርያም**</u> ይባላል;-ትውልድ ገጠሩ ተምቤን ትግራይ ነው። የወያኔ ታጋይ ነበር። በወያኔ የስለላ ክፍል አባል ነበር። ለስለላ ስምሪት ስራ የሰለጠነው ሱዳን ውስጥ ተልኮ ነው። ዛሬ በህይወት የለም። በሻዕቢያ ተገድሏል።ወያኔን ለመጣል ኤርትራ በረሃ ድረስ ለትግል ሄዶ በሰጠው በኤርትራ መርአየ ኩነት (ቴ/ቢዥን) ቃለ መጠይቅ እንዲህ ብሎ ነበር።

"እኔ በዓይኔ ያየሁት አንድ ነገር ነበር! ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን፣ አንድ ጊዜ በዚህ ደብረብርሃን እስረኞችን ለማስፈታት በተደረገው ኦፔረሽን ተሳትፈዋል ብሎ አስወንጅሎ ከባድ ፍርድ እንዲፈረድባቸው በማሰብ፣ ባገር ውስጥ ሚኒስትር ምክትል ሚኒስተር የነበረ ደብረጽየን ገብረሚካኤል የሚባል የሰራውን ሥራ እኔ በዓይኔ ያየሁት ነበር። ፕሪፌሰር በዚህ ዓይነት ሕገ ወጥ ሥራ ተሰማርተዋል ብሎ በታይፕ አርጎ ጽፎ፣ ፊርማቸውን የፕሮፌሰር በሌላ ወረቀት የፈረሙት ፊርማ ኮፒ አደርጎ አስመስሎ በመፈረም እሳቸው ወደ እስርቤት ከገቡ በኋላ፣ ጽ/ቤታቸው የመአሕድ ጽ/ት እንዳለ ዘግቶ ፥ ማኅተም አምጥቶ አትሞ በቀጥታ እንደማስረጃ ብሎ ለፍርድ ቤት አቀረበው። ያ ወረቀት እንደ ዶክዩመንት ተቆጥሮ፣ ፍርድ ቤት ይሄ ጽሑፍ *የሄ ፊርማ*፣ ይሄ ማኅተም የርስዎ ነው ብሎ....ምንም ባልፈጸሙት ወንጀል በእስር ቤት ተሰቃይተው ለሞት ተዳረጉ። እንዲህ ዓይነት አሰቃቂ ግፍ እየተፈጸመ ይህ የታገልክበት ዓላማ በግልባጩ ሲተገበር እያየህ...እኔ በግሌ ለሕሊናየ በጣም ቁስል ነው የፈጠረብኝ። በታሪክም ተጠያቂ የሚያደርግ ስለሆነ የነበረኝም ሁኔታ ከግምት ሳላስገባ የታገልኩለትን ዓላማ የትግራይ ሕዝብ በመሆኔ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የታገለበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተሰው ታጋዮች ወንድሞቻችንና ጓዶቻችን አደራ

ያሉንን ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ዳግም መታገሉን መረጥኩ።“ ***(ኮለኔል ፍስሃ ሃይለማርያም- ኤርትራ ቲ/ቪ- የጽሑፍ ምንጭ የወያኔ ገበና ማህደር- ደራሲ ጌታቸው ረዳ)***

እንግዲህ የደብረጽዮን የመዋሸት ልምድ መቸ እንደጀመረ በቀላሉ ማየት እንደትችሉ ማስረጃ አይተናል። ደብረጽዮን ሙልጭ ካሉ ድሃ ቤተሰቦች እንደመጣ ይነገራል። ከድሃ ቤተሰብ መወለድ ግን ሁለተኛ ዜጋ ነበርኩ፤ትግራይ ተገልሎ ነበር የሚያሰኝ ውሸት እስኪዋሽ አያደርስም። ይህ ውሸት ተራ ውሸት ሳይሆን ፖለቲካዊ ወንጀል ነው። ደብረጽዮን ይህንን ታሪክ የሚበክል፤ የትግራይ ወጣት ትውልድ “አገራችን ነች ከሚሉዋት ኢትዮጵያ” ጋር የሚኖራቸው ቁርኝት የማናጋት ባሕሪው መነሻው እሱ እና መሰል የወያኔ መሪዎች ለኢትዮጵያ ካላቸው ጥላቻ የተነሳ ነጸብራቅ መሆኑን በግሌ የወያኔዎች ንግግር እና ጽሑፍ እንዲሁም ከሚሰጥዋቸው ቃለ መጠይቅ እና ከላይ የተመለከትነው ማስረጃ ሰነድ ያታዘብኩዋቸው አቋማቸው እንደሆነ አውቃለሁ።

ወያኔዎች ለፖለቲካቸው እንዲረዳቸው ሲሉ የሚነዙት “ተገልለን ነበር፤ በአሉታ እንታይ ነበርን” የሚለው እውነታው ሲመረመር መሰረተ ቢስ ነው። ትግሬዎች ከሌሎቹ ጎሳዎች በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እየታዩ “በማንነታቸው” አፍረው እና ተዋርደው” እንዲኖሩ የተደረገበት ጊዜ መቸ ነው? ትግራይ ውስጥ ጨቁኖናል ብለው ከሚወነጅሉት የአማራ ክ/ግዛቶች ውስጥ በትምሕርት እና በጤና ይበልጥ ትግሬዎች ተጠቃሚዎች ነበሩ።

ጎንደርም ሸዋም ወሎም ጎጃምም ጅማም አዲስ አበባም ሓረርም....... ወዘተ ሲኖሩ የነበሩ ትግሬዎች መቸ ነው በማንነታቸው ተንቀው ተገልለው ተጭቁነው ሲኖሩ የነበሩበት ወቅት?

ወደ ሌላ ሳልገባ ይህችን የወያኔዎች **“ተጨቁነን ነበር..ጭቆና ፤ጭቆና...”** የምትለው የሁልጊዜ የትግሬዎች መንቻካ ውሸት ላስምርባት እና አጭር ማስረጃ በመጽሐፌ ውስጥ ከሰፈርኩት ማስረጃ ልግለጽ እና ወደ ደብረጽዮን እንሻገራለን።

የወያኔ ገበና ማህደር በሚለው መጽሐፌ ውስጥ ፋብሪካ በሚመለከት እነሱ የሚሉት ትግራይ ውስጥ አንዲትም አፍብሪካ ይሁን አነስተኛ የግለሰቦች ምርት ሰጪም አልነበረችም ይላሉ።ሃቁ ሌላ ነው ለምሳሌ

ትግራይ (7) ከሰባት ባለይ እኔ የማውቃቸው

- ጎንደር (4) - ወሎ (4) ፋብሪካዎች ነበሩ”። አማራ የሚባለው ክፍል (ጨቆነን ሲሉት የነበረው) በግማሽ ያህል አልነበረውም።

ከመቀሌ ቄራ ድርጅት (ኢንኮዶ በመባል በልምድ የሚጠራው እስራኤሎች ያቋቋሙት የሥጋ ፋብሪካ)፤

የዱቄት ፋብሪካ ፤ በኤርትራዊው አቶ ኤርምያስ (ሥራ አስኪያጁ ልጃቸው የዕብዮ ነበር) የተመሠረተ።

አነስተኛ የእንጨት መሰንጠቂያ ፋብሪካዎችና ውጤቶች (የግል) ብዛት 3 (መቀሌ ብቻ) ማላዊ የባህል ልብስ ፋብሪካ (ወደ መላው ሀገሪቱና ወደ ውጭ አገር የባህል ልብሶችን ኮት፤ ሱሪ፤ ሸሚዝ፤ የሴቶች ልብስና ቦርሳዎች፤ በድርጅቱ የተቀየሱ ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶች፣ በማከፋፈል ብዙ ሠራተኞች ቀጥሮ ሲያስተዳድር የነበረ) ፤

ታይድል በመባል የሚጠራው የዕጣን ፋብሪካ መቀሌ፣ ሽሬ ፣ አክሱም እና ተምቤን በአራቱ ከተማዎች አበጣሪዎችና ጥራት ተቆጣጣሪዎች በመቅጠር (አብዛኛዎቹ ሴቶች እህቶቻችን እና እናቶቻችን) ብዙ ሠራተኞችን የቀጠረ።

የዳቦ መጋገሪያና አከፋፋይ (መቀሌ)

የዘይትና የኑግ መጭመቂያ (ሽሬ አውራጃ)፤

በሌሎቹ ከተሞች የሌለ የመኪና መንዳት ትምህርትና ፈተና የምስክር ወረቀት ዕደላ የሚያከናውን በኤርትራዊው አቶ መስመር ስራስኪያጅነትና ፈታኝነት በጠቅላይ ገዢው በልዑል እራስ መንገሻ ሥዩም የተፈቀደ ለማጅ (DMV) ተብሎ ሲጠራ የነበረ የቤት መለስተኛ አውቶሞቢሎችና የጭነት መኪና ነጂዎች የምስክር ወረቀት በመስጠት በሥራ ላይ እንዲሰማሩ የረዱ የሥራና የትምሕርት ከፋች ተቋሞች ነበሩ።

## ትግራይ ውስጥ

## ከ8 አውራጃዎች ውስጥ ማለትም ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል

5 ት/ቤቶች ነበሩ ።
አማራ በሚባሉ ክፍለሀገሮች
ጐጃም 3 ወሎ 2 ጐንደር 5 (ምንጭ የወያኔ ገበና ማሕደር)

## ከ9-12 ክፍል

ትግራይ 4 (አክሱም ፥ ዓድዋ ፥ ዓዲግራት ፥ መቀሌ ) ፣ ጐጃም 2 (ደብረማርቆስ እና ባሕር ዳር) ፥ ጐንደር 3 (ደባርቅ ፣ ደብረ ታቦር ፥ ጐንደር) ወሎ 2 (ስሂን እና ወልድያ)። (ምንጭ ከእየክፍለሃገሩ ተወላጆች ጠይቄ ያገኘሑት መረጃ- የወያኔ ገበና ማሕደር- ደራሲ ጌታቸው ረዳ)

## የጤና ተቋማትን በሚመለከት፡-

ሰለኽለኻ (ሽሬ) ውስጥ- ሠፊ ሕክምና የሚካሔድበት ዘመናዊ ክሊኒክ:- እንዳስላሴ (ሽሬ) (አንድ ክሊኒክ)
አክሱም ውስጥ- (አንድ ዘመናዊ ሆስፒታልና ክሊኒክ)፣
ዓድዋ (ዓዲ አቡን) አንድ ዘመናዊ ሆስፒታልና አንድ ክሊኒክ (ዓድዋ)
ዓዲግራት (አንድ ሆስፒታል)
መቀሌ (አንድ ሆስፒታልና ክልኒክ)
ተምቤን (ክሊኒክ)
ማይጨው- በጤና መኮንን እና በነርሶች የሚካሄድ አንድ ከፍተኛ ክሊኒክ።

እያንዳንዱ የትግራይ ክሊኒክ ቢያንስ በጤና መኮንን፤ ነርስ እና የከተሞች ምግብ ቤቶች፤ ሉካን ዳና መጠጥ ቤቶች "ሳኒቴሪያን" (የጤነ ተቆጣጣሪ) በመባል በሚጠሩ የጤና ጽዳት አያያዝ የሚቆጣጠሩ የሕክምና ባለሟሎች የተደራ ጀ ነው። በዚህ መልክ ትግራይ 8 አውራጃዎች ሲኖሯት በወቅቱ እያንዳንዱ ከላይ የተመለከቱ ት ተቋማት የያዘ ነበር። (አሁን ቡና ቤቱ (ብርጭቆዎች) በየጠላ ቤቱ እየዞረ መጠጫ

ምኒሊኮቹ በሳሙና እና በውሃ በጽዳት መታጠባቸው የሚቆጣጠር ሳኒቴርያን /ክፍል መኖሩ እጠራጠራለሁ። ***(ምንጭ የወያኔ ገበና ማሕደር- ደራሲ ጌታቸው ረዳ)***።

ይህ ነው "ትግሬዎች" ተገልለን ተነጥለን አሉታዊ ኑሮ እንኖር ነበርን ወዘተ..እያሉ አማራውን በሓሰት ሲወነጅሉና አሁንም እየዋሹ የምናደምጣቸው። በማንነታችን ተጨቆንን የሚሉት አስገራሚ የሚሆነው ደግሞ 'ባንድ ዘር ያነጣጠረ ጥቃት ሲፈጽሙ' መኖራቸው እንደማናውቅ አድረጎ ደብረጽዮን ያለማፈር በሕዝብ ፊት ስለ ማንነት እና ስለጭቆና እና ውርደት ሲናገር ማድመጥ የሚገርም ነው።

በታሪካችን እኛ ትግሬዎች እርስ በርስ ስንነታረክ ባለፉት ወቅቶችም ሲገዳደል እና ሲናናቅ መሳፍንቶቹ እርስ በርሱ በትውልድ እና በአውራጃ እንዲነጣጠል ሲያደርጉ፤ ለጣሊያን ሲያድሩ፤ ተጠያቂ የሚያደርጉት አሁንም ምኒሊክን/ አማራውን/ ኢትዮጵያን/ ሰንደቃላማን ነው። ለውርደታቸው ሁሉ ተጠያቂው ሌላ ክፍል ነው። በቋንቋችን መጻፍ ተከልክለናል ሲሉ ውጭ አገር ሲኖሩ የነበሩ ትግሬዎቸ እንኳ ቋንቋቸውን ማሳደግ ሲችሉ እና በቋንቋቸው መጻፍ የሚችሉበት ሌላ ዓለም እየኖሩም ቢሆን ያበረከቱት ኢሚንት ነው። የነሱን ደካማ ገመና ሳይፈትሹ ሌላውን መጀመሪያ ተወቃሽ ያደርጋሉ።

ሌላ ቀርቶ የሃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሆነው ልክ ፖለቲካውን በድብቅ ጽፈው በሌሊት በየመንገዱ፤ በየት/ቤቱ ሲረጩት እንደነበረው ሁሉ የትግሉን ዕድል ተጠቅመው በቋንቋችን እንዳንጽፍ ተከልክለን ነበር የሚሉትን ትግርኛ ቋንቋን እንኳ በድብቅ ሌላ ዓለምም ሆነው አገር ውስጥም ሆነው የትግርኛ ስነ ጽሑፍ እየጻፉ የተመኙትን መጻፍ ለማስተዋወቅ ሳይችሉ ሲቀሩ ለውሸት እንዲመቻቸው ንግግራቸው ሁሉ ቋንቋችን "ሃይለስላሴ ፤ ምኒሊክ፤ ደርግ…. አግዶናል' ነው የማምለጫ ምክንያታቸው። በሕግ የታገደው የማኦ ኮሚኒስት ማኒፌስቶ ግን እንደ አሸን እየበተኑ፡ ኪሳቸው ውስጥ ሸሽገው በየሻይ ቤቱና ጠላ ቤቱ እንያዛለን ብለው ሳይሰጉ ሲቦተልኩበት እና ሲጨቃጨቁበት፡ 'የራሳቸውን ስነጽሑፍ' ጽሑፍ ማሰራጨትና ማሳደግ ችል ብለው ሰንፍናቸውን ለመሸፈን በሌላ ሰው ያላክካሉ።

አውነት ነኝ የምላችሁ፡ ራሳቸውን ተጠየቂ ማድረግ አይፈልጉም። በእዛው በነገሥታቱ ዘመን ምን የሚሉት ዲሞክራሲ ይጠብቁ እንደነበር ሳስበው ለኔ ይገርመኛል። የትግራይ ምሁራን ከታገድን ውንጀላ ሌላ ራሳቸውን መወቅስ አይፈልጉም። ነገድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝም በትግርኛ ሲጽፉ አላየሁም። ሁሉም ነገር <u>**ያለ ትግል**</u> በብር ማንኪያ እና በብር ሳሕን እንዲያቀርብላቸው ሃይለስላሴን ፤ ምንሊክን ይወነጅላሉ። በዘመኑ የነበሩ የትግራይ ምሁራን አጼ ዮሃንስ ሲነግሱ በነበሩበት ዘምንም ትግርኛ መጻፍ ሲቻል ያንን ሳይደረጉ አሁንም ውንጀላቸው ያው ወደ ፈረደበት አማራ እና አማርኛ ቋንቋ ነው። አረሞዎቹም ትግሬዎቹም የሚወነጅሉት ዘፈናችን አድማጭ አላገኝም ምክንያቱም የአማርኛ ዘፈን "ዶሚናንት ሆኖ" ገበያው እየነጠቀን ነው፡ እያሉ ኦሮሞቹም ትግሬዎቹም የተፈጥሮ ጣዕም የተለገሰውን አማርኛ

ዘፈን እና እስክስታ ማራኪነቱን እንዲለውጥ ይወተውታሉ። ውንጀላቸው ሁሉ መጠን የለውም። ተፈጥሮ የለገሰውን ሁሉ በጨቋኝነት /በዶሚናንትነት/ ይከሱታል። ተፈጥሮ የበደለውንም መሬት ለመሃንነቱ ምክንያት ሲሰጡ "እገሌ የሚባል ስርዓት ስለ ጨቆነን ነው" ይላሉ። ስልጣን ሲይዙ ደግሞ የለፈፉለት የሰው መብት ጥበቃ እና እኩል የሃብት ክፍፍል ልፈፉ እንደለፈፉት ሳይሆን 'ግድያ ፤ ጭፍጨፋ ፤ ማሰቃየት" እያስፋፉ ሃብት እየዘረፉ 'ሁሉም ነገር ወደ ትግራይ ማቋቋም' ዘመቻቸው እየተመሩ በአሳፋሪ ድምዳሜ ስርዓታቸው ተደመደመ።

አጼ ዮሐንስ እና አሉላ የጉራዕን እና የዶጋሊን ድል ተጠቅመው ምጽዋን መያዝ ሲችሉ ያንን ድል ሳይጠቀሙበት ወደ ኋላ ሲመለሱ እና ጣሊያን መሰረቱን ሲጥል አሁንም ተጠያቂ የሚያደርጉት ያው ምኒሊክን/ሸዌዎችን/ ነው። ምንሊክ ዓድዋ ላይ የተገኘው ድል ተጠቅመው ወደ ኤርትራ ሄደው ጣሊያን ባለማስወጣታቸው ኤርትራ ሄደች ብለው ምንሊክን ሲከስሱ፡----- አጼ ዮሐንስ እና አሉላ ግን የጉራዕን እና የዶጋሊን ድል ተጠቅመው በማግስቱ ምጽዋን መያዝ ሲችሉ ያንን ድል ሳይጠቀሙበት በመቅረታቸው ጣሊያን ወደ መሃል እንዲቆጣጠር ዕድል አገኘ ሲባሉ፤ መልሳቸው ዛሬም "ንጉሡ ዱርቡሽ ለመውጋት ወደ ጎንደር ስለሄዱ ነው መልሳቸው" (ሌላውን አጋጣሚ ዕድሎች ሳናናሳ በዚህ መልሳቸው እንኳ ስንመለከት ምንም እንኳ ጊዜው የዱርቡሽ ወሬ ሳይሰማ የሁለት ወር ልዩነት እና በቂ ጊዜ ቢኖርም)። የሚገርመው ደግሞ ከዶጋሊ እስከ ምፅዋ ያለው ርቀት 10 ማይል ወይንም 16.7 ኪ/ሜ ነው። በመኪና የ 18 ደቂቃ ጉዞ ሲሆን በተዋጊ እግረኛ በጥንቃቄ ቢኬድ የሁለት/ሦስት ሰዓት ጉዞ አይሆንም። (ከዓድዋ ወደ ምፅዋ ያለው ርቀት እና፤ ከዶጋሊ ወደ ምፅዋ ያለው ርቀት ጠላትን ለመምታት ያለው ልዩነት እና አስቸጋሪ እና አመቺነቱን እራሳችሁ ፍረዱት። ያውም ጣሊያን በመላዋ ኤርትራ ተንሰራፍቶ በነበረበት ወቅት ለምኒሊክ ተዋጊዎች ሊገጥም የነበረው ኤርትራ በናንዳ እና ጣሊያን ሠራዊት ያለው ስፋት እና አስቸጋሪነቱን ፍረዱ ) በሁለቱ የቦታ ርቀት እና የቦታ የተዋጊ ምሽጎች ብዛት እና ሽፋን ያለው ልዩነት ይታያችሁ።

አጼ ምኒሊክ ከጣሊያን ጋር በደብዳቤ ሲሞዳሞዱ ነበር እያሉ ሲወነጅሏቸው፤ በሌላ ወገን ድግሞ አጼ ዮሐንስ ከጣሊያን ጋር ለምንስ የደብዳቤ እና የሞዳሞዱን ባሕሪ መረጡ ተብለው የመልስ ምት ሲጠየቁ 'መልስ የላቸውም። ወያኔዎች እና የትግሬ ምሁራን ውዥምብራም ውሸት በዚህ ብቻ አላቆሙም፤ ምንሊክ በትግሬዎቹ ለዕርዳታ ጥያቄ ተጠይቀው ትግሬዎችን ነፃ ለማውጣት ከሸዋ ገስግሰው ጣሊያንን ዓድዋ ላይ ድል መትተው ትግሬዎች ከጣሊያን ቀንበር ነፃ ካወጥዋቸው በኋላም "ምኒሊክ" ወደ ትግሬ የመጣው ትግራይ በወቅቱ በመላ አገሪቱ በላይ ብር ስለነበረ የትግሬን ኗሪ ብር ለመዝረፍ ነው የመጣው" ይላሉ። አለፍ ብሎም "ምኒሊክ የመጣው ትግሬዎችን ለመከፋፋል እና ማንነታችን ለመደቆስ ነው" እያሉ ወንጅለዋቸዋል።

## ***የትግሬዎች ውሸት በዚህ አላበቃም።***

አጼ ዮሐንስ የአጎታቸው ልጅ የሆኑት የራስ አርአያ ድምጹ ልጅ (የዮሓንስ እናት (ወ/ሮ ስላስ) እና የደበብ አባት ‘ራስ አርአያ ድምጹ’ እህት እና ወንድም ናቸው) ስለ ደጃች ደበብ አርአያ ለጣሊያን ንጉሥ የጻፉት ደብዳቤ ስንመለከት እንዲህ ይላል፡- **“ደጃጅ ደበብ ጣልያኖች ወዳጆቼ ናቸው እና ውደዱልኝ ብየ ብላቸው እምቢ ብለው ከአንገት በር አድፍጠው ተሰልፈው ቆይቶው ተዋጉኝ ፡ እግዚአብሔር ቸርነት በእመጽዮን አማላጅ እና በእርስዎ ጸሎት ድል አደረግኋቸው እሳቸውም ሞቱ።” (ይድረስ ለጎጠኛው መምህር -ደራሲ ጌታቸው ረዳ ገጽ 230 (Archivio Storic? (Ethiopia) XV 1895 -Roma)** ሲሉ ለሮማ ንጉሥ ኢምቤርቶ ደብዳቤ ሲጽፉ ግን ዮሐንስ ትግሬ ስለሆኑ ባንዳ አይባሉም። ምኒልክ ለጣሊያን ፍቅር የሚገልጽ ተመሳሳይ ደብዳቤ ሲጽፉ ግን ምኒልክ ‘ባንዳ’’ እና የጣሊያን ወዳጅ ነበሩ ይሏቸዋል።***(ይድረስ ለጎጠኛው መምህር ገጽ 226- ደራሲ ጌታቸው ረዳ 2002 ዓ.ም)***

ራስ መንገሻ የወላጅ አባታቸው የዮሐንስ “የፈረስ ኮርቻ” ለጣሊያን ሲሸልሙም ሆነ፤ በራሱ እና በጣሊያኖች መካካል የተፈረመው ውል “ራስ (መንገሻና ዤኔራል ጋንዶልፊ) **“የኢጣሊያን መንግሥት የሚጠላ ለራስ መንገሻ ጠላት ነው። የኢጣሊያን መንግሥት የሚወደው ወዳጅ ነው። ራስ መንገሻ የኢጣሊያ መንግሥት ይወደዋልና ያከብረዋል። ህዳር 29 ቀን 1884 ዓ.ም” (Historica Diplomatica…Rosetti PP.108-111”** ***(ይድረስ ለጎጠኛው መምህር ገጽ 226- ደራሲ ጌታቸው ረዳ 2002 ዓ.ም)*** የሚል **“የአገር ክሕደት”** የሚያሳይ ውል በትግሬዎች ሲፈረምም ያው የትግሬ ምሁራን ውንጀላቸው በሌላው ክፍል ብቻ ነው።

ውረደት ጭቆና፤ ማንነት… የሚሉዋቸው መገለጫዎች ሁሉ በራሳቸው ገዢዎች ሲፈጸሙ ምንም አይደለም። በሌሎች አድራጊነት በትግሬዎች ላይ ሲፈጸም ግን “አድልዎ፤ አሉታ ፤ መገለል፤ ሁለተኛ ዜጋ ….” የሚል ሓረግ ቅጥያ ይሰጠዋል። ብታምኑም ባታምኑም በእነዚህ የታሪክ አተላዎች ምክንያት እኔ እንደ ትግሬነቴ እንደዛሬ ትግሬነቴን ያስጠላኝ የታሪክ ዘመን የለም። ምን ቢደረግ ነው እንዲህ ያለ ወገንተኛ እና የውሸት ጎርፍ ማሰቆም የሚቻለው? ውሸታቸውን ከማጋለጥና ለእውነት ስል እራሴን በውሸታሞች ምላስ ለስድብ እና ለመገለል ከማጋለጥ ባሻገር ምን ማድረግ እችላለሁ? ምንም!!

ደብረጽዮን ዛሬም የሚከስሰው ያው ኢትዮጵያን እና አማራውን ነው። ትግሬውን እንዲህ አደረገው፤ ምኒሊክ ከጣሊያን ጋር ሲሞዳሞድ ነበር…ነው… ክሳቸው። እኛ ከሌለን በሚኒሊኮች ትጠፋለህ ወዘተ…እያሉ የውሸት ጋጋተው ሕዝቡን ይመግቡታል። እነ ደብረጽዮንም ሆኑ ከነሱ በፊት የነበሩ የትግራይ ገዢዎች በራሳቸው ጎሳም ሆነ በሌሎቹ ጎሳዎች ተመሳሳይ ድርጊት እንደፈጸሙ ማስረጃ ሲቀርብ ግን እንደማምለጫ የሚጠቀሙት መሳርያ “በውሸት ሕዝብን ማደናገር” ነው።

“ወያኔዎች ሰውን ከነ ነብሱ ጉድጓድ ውስጥ ከትተው፤ሰውነቱ ተልቶ ትሎች በጆሮው እና ባፍንጫው በአፉ እየተርመሰመሱ በቁሞናው በትል እየተበላ ቀዳው እና አጥንቱ ፈርሶ የሲኦል ሞት እንዲሞት ያደርጉ ነበር” የሚል ክስ ሲቀርብባቸው (አሞራ የሚለው መጽሐፍ በግደይ ባሕሪሹም ይመልከቱ) ወይንም አረጋውያንን እሳት አንድደው ገላቸው እየለበለቡ ሲያሰቃዩዋቸው ነበር ለሚለው ክስ መልስ የላቸውም። የወያኔ ገበና ማሕደር መጽሐፍ ልጥቀስ እንዲህ ይነበባል

“እኔን ለማቃጠል። ቀጭን እንጨት እና የሚቀጣጠል ሳር ዙርያየ ደርድረውበታል።
ሊያቃጥለኝ የቆመው መርማሪየ ሰውየ እጁን ዘርግቶ በመለካት “አንድ ክንድ” ከለካ
በኋላ እኔን ከዛፉ ጋር የፍጢኝ አስሮ ማገዶውን በዙርያየ ከምሮ የፍጥኝ እንደታሰር
ኩ ከዛፉ ዙርያ “ኩምትር” ብየ እንድቀመጥ አዘዘኝ። በአንድ ክንድ ርቀት በዙርያየ የ
ተከመረው ሳር እና ቀጫጭን እንጨት በሳር አቀጣጥሎ እሳት ለኰሰበት። እንጨቱ
መጀመሪያ ጭስ ማውጣት ጀመረ፤ ሳሩም መቀጣጠል ጀመረ ጭሱ አፈነኝ። ጭሱ
ሲያፍነኝ መተንፈስ አልቻልኩም ጨነቀኝ። ጥልቅ ባሕር ውሃ ውስጥ ጠልቀህ ተው
ጠህ መውጫ እናዳጣ ሰው ነው ትንፋሽ አጥሮኝ የተሰማኝ። ጭሱ በዙርያየ እንደ ጉ
ም እየተልመለመለ ሲነሳ መርማሪየ  አሳቱ ይበልጥ እንዲቀጣጠል ቆሞ ይቆጣጠራል
፤እኔኑም ያየኛል። ጭሱ ወደ እኔ እየገፋ እየበረታብኝ “አፈነኝ”። ሲያፍነኝ መሳል፤
መተንፈስ አልቻልኩም። በጣሙን ጨነቀኝ። ነፋሱ በርትቶ ጭሱን ካስወገደው በኋ
ላ፡-
እንጨቱ እየተቀጣጠለ ወደ አሳት ተቀይሮ መንደድ ጀመረ። ነፋሱ ነበልባሉን በሁሉ
ም አቅጣጫ ወደ እኔ ዙርያየ ይገፋው ስለነበር ገላየን መለበለብ ጀመረው።……..”

*(የቃለ መጠይቁ ምንጭ የወያኔ ገመና ማሕደር”- ደራሲ ጌታቸው ረዳ እና የደጀን ራዲዮ አዘጋጅ ዶ/ር ሃይለማርያም አበበ)።*

በማለት ከላይ ያነበባችሁትን የሰው ልጅ እንደ በቆሎ እሳት ውስጥ ሲጠበስ፤ ያውም አረጋውያን ሽማግሌዎች በአሰቃቂ የግፍ ድርጊት ሲካሄድባቸው ወያኔዎች ሁሉንም የማድረግ መብት አለን ይላሉ። ከላይ ያየነው ግፍ የተካሄደባቸው ፊታውራሪ ገዛኢ ረዳ ሲሆኑ፡ የተፈጸመውም ትግራይ በረሃ ውስጥ በወያኔዎች የጫካ ምርመራ ክፍል ነው። ወያኔዎች ስላለፉት ስርዓቶች በትግሬዎች ስለደረሰው ስለ የማንነት መብት ግፍ እና ጭቆና ሲያወሩ፤ እነሱ ለፈጸሙት አሰቃቂ ግፍ ለምን እንደተፈጸሙት ሲጠየቁ ግን መልሳቸው “ትግሉ የጠየቀው አሰራር ስለነበር በወቅቱ መፈጸም ነበረበት ካልሆነ እዚህ ባልደረስን” የሚል የሌባ

ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ ዓይነት የሚል መልስ ይሰጣሉ። ለወንጀላቸውም ይቅርታ አይጠቁም፤ ምክንያቱም “ትግሉ ዳር ለማድረስ የተደረገ ግዳጅ ነበር ነውና” የሚል መልስ ይሰጣሉ።

ይሕ አሰቃቂ ምርመራ እንዲካሄድ ያደረገው መርማሪ ደግሞ የወያኔው አየርፎርሱ ጀኔራል አበበ ተክለሃይማኖት (ጆቤ) ነው። አበበ ዛሬ የፖለቲካ ተንታኝ እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህር ነው። በጆቤ መርማሪነት የተካሄደው ጭካኔ እንደተፈጸመ በራዲዮ የሰጡት ቃለ መጠይቅ በግል ሳወያየቸውም ብዙ ጊዜ ይህንን ግፍ እና ከሳቸው ጋር አብረው ታስረው እና በእሳት ተለብልበው የሞቱ በራሴ ቤተሰቦች ላይ የተፈጸመ ወንጀልም ጭምር ነግረውኛል። ታዲያ እነ ደብረጽዮን ሰለማንነት እና የሙብት ረገጣ ሲያወሩ ሓፍረት የሚባል የላቸውም።

በማንነታችን አፍረን ነበር…የኢትዮጵያ ታሪክ ጨቁኖን ነበር… የሚለው ደብረጽዮን መነሻው ምንድ ነው? ለሚለው ከወያኔነቱ ሌላ ‘ደብረጽዮን ከትግራይ እና ከኤርትራዊያን ቤተሰቦች የተወለደ’ ከመሆኑ ጋርም ለኢትዮጵያ ያለው ጥላቻ ግፊት ሰጥቶታል። በዚህ ትችት ርዕስ የተመለከተው የትግራይ ሕዝብ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ሲታይ ነበር የሚለው ውሸት ያስተጋባው ባለፈው ሰሞን ነሓሴ 2010 ዓ.ም መቀሌ ከተማ በተካሄደው ‘አሸንዳ’ በተባለው በዓል ለአሸንዳ ተሳታፊዎች እና ተከመልካቾች ባደረገው ንግግሩ ነው።

ደብረጽዮን ያለ ምንም የታሪክ ይሉኝታ ያስደመጠን በትግርኛ ያስተላለፈው ይህንን ውሸቱን ሳደምጥ የተሰማኝ ስሜት ከመገረም አልፌ ፤ የወያኔዎች የውሸት ባሕሪ ድግምግሞሽ ስለገረመኝ “ሰው ስንት ጊዜ ይዋሻል?” የሚል ጥያቄ ጫረብኝ። በመጽሐፍ ቅዱስ በ10ቱ ቃላት ውስጥ የቁጥሩን ቅደም ተከል ባላስታውሰውም “በሃሰት አትምስክር” የሚል አለ። ወያኔዎች በኮሚኒስቶች መመሪያ ሕግ የሚያምኑ እና የመጽሐፍ ቅዱስ አማኞች እንዳልሆኑ ባውቅም፤ ውሸት መልክ አለው ይባላል። መጠን ሲባል ከባድ እና ቀላል ለማለት ይመስለኛል። እንደ ሰው ሁላችንም ብንዋሽም ብንሳሳትም ‘ስንዋሽ እንዲህ ያለ ለመቀበል የሚከብድ ውሸት ግን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ሕዝብ ከሌለ ዋሾች እንዲሁ ከመሬት ተነስተው ሊዋሹ አይችሉም የሚል እምነት አለኝ።

በትግራይ ሕዝብ ፊት ቆሞ “አንተ ሁለተኛ ዜጋ ነበርክ” “ወያኔ የትግራይ ሕዝብ መብት አስጠባቂ ነው ፥ ወያኔ አልገረፈህም፥ አላሰቃየህም፥ አልገደለህም..” የጨቆኑህ ያሰቃዩህ አማራዎች ፥ ኢትዮጵያ እና ሰንደቃላማቸው ናቸው፡’ ብሎ ሲናገር ከደብረጽዮን ይልቅ የተገረምኩት በትግራይ ሕዝብ እና ምሁር ላይ ነው። ሁለተኛ ዜጋ ነበርክ ተብሎ ሲነገረው ‘ያለ ምንም ተቃውሞ (ያለምንም ሪአክሽን) አድምጦ ዝም ሲል ሕዝቡም ሁለተኛ ዜጋ ነበርኩ የሚል እምነት እና ወያኔ አልበደለኝም የሚል ስሜት አለው ማለት ነው። ያ ባይሆን ኖሮ ይኼኔ ብዙ ተቃውሞ መደመጥ ነበረበት።ግን አልሰማሁም። ለዚህ ነው ጊዜ ልስጥ እና እስኪ ከትግራይ ሰዎች ተቃውሞ ካለ ላድምጥ ብየ ወዲያውኑ መልስ ላለመስጠት የዘገየሁት።

ደብረጽዮን ትግሬዎች <u>በማንነታችን እንድናፍር የተደረገበት በቋንቋችን እንድንሸማቀቅ የተደረገበት የታሪክ አጋጣሚ ነበር</u> ሲል ኢትዮጵያን ይከስሳል። ለመሆኑ ይህ የሚከተለው ግጥም የገጠሙት አማራዎች ናቸው ወይስ ኢትዮጵያ የምትባል በትግሬዎች ታሪክ እየተወነጀለችው ያለቺው አገር ነች የገጠመቺው? እስኪ እንመልከተው ይህንን ግጥም፤-

***"ዓድዋ አኽሱም ሽረ ጹሩያት ተጋሩ***
***ራያ እንደርታ ተምቤን ኀረቤት አምሓሩ"***

**ትርጉም**

***"ዓድዋ አክሱም እና ሽሬ የጠሩ ትግሬዎች***
***ራያ እንደርታና ተምቤን ያማራ ኀረቤት"***

በማለት በትግራይ ውስጥ የትውልድ አዉራጃና አካባቢ፤በጎጥ እና የወንዜ ልጅ፤ የደም ያጥንት የዘር ጥራትና ቆሻሻነት የበላይነትን በሚያንጸባርቅ የናዚዎች እና የፋሺስቶች ቅስቀሳ እና ትምክሕት የሚገልጽ ግጥም ገጣሚው እራሳችን ትግሬዎች ነን! አይደለም እንዴ? ታዲያ በራሳችን ማንነት የዘመትን ሰዎች በምን ሞራል ነው ሌላውን በማንነታችን ተጭቁነናል ተሰድበላል አፍረናል፤ተገልለናል፤ በአሉታ ታይተናል .. እየተባለ በሕዝብ ፊት ሌላውን ለመወንጀል የሚዋሸው? በዚያ ምክንያት ይሆን ሦስቱ አውራጃዎች የጠሩ ትግሬዎች ስለሆኑ እንደርታዎች እና እነዚህ የተጠቀሱ የአማራ ኀረቤቶች ተብለው የተገጠመላቸው አካባቢዎች የራሳቸውን የትግርኛ ልሳን ጥለው በአክሱም ሽሬ ዓድዋ እና ኤርትራ ትግርኛ መናገር የጀመሩት?

በየፓልቶኩ እና በትግራይ የሚሰራጩት ራዲዮኖች፤ቲ/ቪ፤ መጽሔቶች ሙዚቀኞቻቸውን፥ ገጣሚዎችን....ብትመለከቱና ብታደምጡ ፡ በጣም ትገረማላችሁ!!! ተምቤኖች ፥ ማይጨዎች ፥ አጋሜዎች፥ እንደርታዎች መሆናቸውን የምታውቁዋቸው "እነዚያን" ለመሆን ሲከጅላቸው **<u>ከምላሳቸው ጋር የሚያደርጉት ትግል ባያስታውቅባቸው እንደርታዎች መሆናቸውን ለማወቅ ያዳግታል</u>**። እኮ ለምን እንዲህ ሆነ? መሸማቀቅ ፥ በራስ ልሳን ማፈር ፥ መስሎ መሄድ......ማንነትን የመሸሽ ክስተት ምን አመጣው? ያውም በዛሬው በትግሬዎች ንግሥና ዘመን!

የነዚህን አውራጃ ባሕላዊ ልሳን ማን ነው እየተጫነባቸው ያለው? አማራው ወይስ ከ "አሽዓ" የመጡ የወያኔ ትግሬ መሪዎች? ትግርኛ ትግረኛ ነው፤ የሚለው የማታለያ (*ሸዋዳ) ክርክር ካሁን በፊት በስፋት ስለጻፍኩበት እዚህ አልደግመውም። የአማራ ኀረቤቶች ላለመባል ለመሸሽ ከሆነ የማንም ይሁን የማንም ቋንቋ ልሳን ተናጋሪ ከቅጥያ የማንኳሰስ ልጠፋ ነፃ ስለማይሆን ራስን እና አካባቢውን መስሎ መኖር የማንነት ምልክት ስለሆነ ራስን ከመፈተሽ

እና ሌላውን ከመወንጀል መቆጠብ ነው። አነጎች ‘ጋላ’ የሚለው መጠሪያ ‘ስድብ’ ነው ብለው ‘ኦሮሞ’ በሉን ሲሉ “ኦሮሞዎች” ኦሮሞ ስለተባሉ ከንቀት እና ከስድብ ነፃ ይሆናሉ ብሎ መመኘት የሰው ልጆች ባሕሪ ያለማወቅ ነው። ባጠቃላይ አጭበርባሪዎች ሰራንልህ ብለው በሕዝቡ ሕሊና እየተጫወቱ ለመጻደቅ የሚጠቀሙበት ማጭበርበርያ ስልታቸው ነው። ይህ ሁሉ ውሸት ለምን ነገሰ? ስንት ጊዜስ መዋሸት ይቻላል?

ሰው ስንት ጊዜ ይዋሻል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ስፈልግ አንድ የስነ ልቦና ጥናት ምሁር ባደረገው ጥናት እንደሚለው ከሆነ ሰው በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ 1.65 ጊዜ ወይንም ከዚያ በላይ ይዋሻል ይላል። ይህ ጥናት “አሸረጅ” ከሚባሉት ማለትም “ተራ ዜጋ” እንጂ የፖለቲከኞችን አይጨምርም። እነሱ ጋር ሲሆን አጅግ ከፍ ያለ እንደሆነ እገምታለሁ።

የኛዎቹ ዋሾች ለየት የሚያደርጋቸው ምላሳቸው ብቻ ሳይሆን እጆቻቸውም በሰው ደም የተቀቡ ስለሆነ ሲዋሹ የተመዘገቡት የውሸት ሚዛኖች ያልፉዋቸዋል። የዓለም ዘፋኞች ለውሸት ያበረከቱት አስተዋጽኦ ይሁን አይሁን ባላውቅም ውሸት ተቀባይነት እያገኘ ሄዷል። **“አወሻሸትህን ወደድኩት”** የሚሉ ዘፋኞች አሉ፡ (I love the way you lie) የሚሉ ዘፈኖች ተቀርጸው ለገበያ ሲቀርቡ ከፍተኛ ገበያ አላቸው። የኛ ዘፋኞችም እንዲያ ያለ ዘፈን እንዳላቸው አሁን ስሙን ባላስታውሰውም አድምጫለሁ።

የትግራይ ሕዝብ እንዲህ ያለ ውሸት በላዩ ላይ ሲዋሸበት እንዴት ሊቀበለው ቻለ የሚለው የስነ ሉቦና እና የኣእምሮ ሊቃውንት የመልሱት። ይህ ሁሉ የተማረ ትግሬ ፤ ከትግራይ ወደ አዲስ አበባ የመጣ የትግራይ ትወላጅ፡ ከጥላሁን ግዛው ከብርሃነ መስቀል እስከ እነ በረከት ሃብተስላሴ እስከ ሰንቱ የትግራይ እና የኤርትራ ተወላጅ ዲታ/ታጁር / የናጠጠ ነጋዴ ፥ አስመጪ እና ላኪ ፥ ባለ ዜታው የጭነት መኪና ፥ ስንቱን ሻምበል ፥ ሰንቱን ጀኔራል ፥ ስንቱን ኮለኔል፥ ስንቱን ዶክተር ፥ ስንቱ ደራሲ ፥ ስንቱን ዳኛ ፥ እና ጋዜጠኛ ፥ ስንቱ ተዋናይ እና ታዋቂ ሙዘቀኛ ፥ ስንቱ የትግራይ ተወላጅ ሹመኛ እና ሓብታም ስም ዝርዝር ጠቅሰን ያልቃል? ትግሬዎች በምን መልኩ ነው “እንደ ደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች” በማንነታቸው ተዋርደው እና አፍረው በሁለተኛ ዜጋ ይታዩ እን አሉታዎ ዜጋ ሲታዩ የነበረው? በየትኛው የታሪክ ዘመን? ለመሆኑ ወላጆቻችን መስርተዋታል የሚሏትን ኢትዮጵያን ያውቁዋታል? አያውቁዋትም። እንዲያ ባይሆን ኖሮ ስብሓት እንዲህ ባላለ ነበር፡_

**“ያቋቋምነውን ኮንስቲትዩሽን የሚቀማን ፤ የሚያደናቅፈን ሃይል ከመጣ እንገነጣጠላለን። እኛ ይኼ ኮንስትትዩሽን ከተቀማን… እንደገና እደግመዋለሁ! እኛ ይኼ ኮንስትትዩሽን ከተቀማን ወይንም ለቀማን እንደገና ጦርነት እናዉጃለን! ወደ ውግያ እንኄዳለን ! ወይንም ደግሞ ተገነጣጥለን የየራሳችንን መንደር እንይዛለን።፡ይህ ኮንስትትሽን የማንነታችን መለኪያ ስለሆነ ማንነታችንን የሚቀማን ከመጣ “እንደነት” የሚባል ነገር አይኖርም!”**

በማለት አለቃቸው ስብሓት ነጋ ነግሮናል። (**“ዲሞክራቲክ ፎረም ፎር ዲሞክራሲ ኤንድ ሲቪሊቲ”** በታባለ የወያኔ አሽቃባጭ ፓልቶክ ቀርቦ ከተናገረው ቃለ መጠይቅ የተገኘ - አውድዮ (የድምፅ ማስረጃ ወደ ጽሑፍ የተረጎመው ‘ይድረስ ለጎጠኛው መምህር- ደራሲ ጌታቸው ረዳ - ገጽ 142)

አሁን ናዚያዊ ሕገመንግሥታቸው የሕዝብ ቅዋሜ ደርሶት በመቀማት ላይ ነው። ስብሓት ያኔ ከ8 አመት በፊት የተናገረውን ትንቢት እውን ለማድረግ ይሆን ደብረጽዮን ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለትግራይ ሕዝብ አስሬ በመዋሸት ዘመቻ ተጠምዶ ሲዋሽ ያደመጥነው?

የሕዝቡን በተለይ የወጣቱን ሕሊና ለመጥለፍ ይህ ሀሉ ተደጋጋሚ ውሸት እየተዋሸ ሲደመጥ የሚያሳየን እውነታ “የትግሬ ሕዝብ ያዋጣናል ብሎ እስካሁን ድረስ ወያኔዎችን አቅፎ ደግፎ እንደተከላከለላቸው ሁሉ ዛሬም ያንኑ ቀጥለውበታል የሚያስብል ነው”። ሕዝቡ <u>“አይዞኹም ናይና!!!</u> <u>**(የኛዎቹ - አይዟችሁ)**</u> እያለም እየዘፈነላቸው ነው። እንዲህ የሚሉም ጥቂት ካድሬዎች ናቸው የሚለው ማጃጃያ በኔ በኩል አልቀበለውም። ምክንያቱም በዛው ልክ ተቃውሞ ሲያስደምጠን አልሰማንም ፥ አላየንም። <u>**አይዟችሁ የኛዎቹ**</u> የሚለው የኳስ ጨዋታ ቡድንተኛ መፈክር በተወጣተረ ፖለቲካ ውስጥም ጠቀሜታ አለው ተብሎ ለዕልቂት ማበረታቻ የሚያገለግል መፈክር ከሆነም ጠቀሜታው አብረን እናየዋለን።

ምንም <u>**ቢዋሹ**</u> ፤ ምንም <u>**ቢገድሉ፤**</u> በግፍ የታፈሰ መንገደኛ ታሳሪን <u>**ቤተሰብ ተጥረቶ ውክልና ሳያረጋግጥ ሆስፒታል ተወስዶ ባስገዳጅ ሁለት እግሩ እንዲቆረጥ አድርጎ እንደገና ቁስል ሳይድን ዝቅዝቅ ሰቅሎ በመደብደብ የተካፈሉ ትግሬዎች**</u> ፥ <u>ምንም **ቢዘርፉ፤ የእስረኛ ብልት ቢያኮላሹም ፤ ምንም የፈለገው ወንጀል ይሰሩ**</u> “<u>***የኛ ናቻው”***</u> እና አሳልፈን አንሰጣቸውም ሲሉ እንደ እነ አብርሃ ደስታ የመሳሰሉ የትግራይ ወጣት ምሁራኖችም እየተከላከሉላቸው ነው።

በእነ ደብረጽዮን ውሸት እንደ <u>የበጋይት *የከብት*</u> በ<u>**አይዞህ የኛ**</u> <u>“የመንጋዎች”</u> መፈክር” በሚደወልለት ቃጭል እየተመራ በመክነፍ ላይ ያለው ያልተገራ ጉዞ <u>**ለትግራይ ሕዝብ የሚጠቅም መፈክር ከሆነ**</u> መሰንበት ደግ ነው፡ እንሰንብትና ውጤቱ እናየዋለን። በወንጀለኞች ውሸት እየተነቃቃ “የትግራይ ሕዝብ ዜጋነቱ በአሉታዊ ሲታይ ነበር እየተባለ ፥ ትግሬዎች ከደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች ጋር የሚያመሳስለው የደብረጽዮን ውሸቶች እና እንበታተናለን የሚሉ የወንጀለኞቹ መፈክሮች ትግሬዎች የወያኔዎች የውሸት ምሽግና መከታ መሆን የለባቸውም።

ጌታቸው ረዳ (Ethiopian seamy አዘጋጅ)